# የአዲስ ኪዳን መሠረታዊ ትምህርት

**ወንጌላት**
**የሐዋርያት ሥራ**

**የጥናቱ/የትምህርቱ መግለጫ**

የመጀመሪያዎቹ አምስት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የኢየሱስን ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞትና ትንሣኤ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኑ አጀማመር ስለሚተርኩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ መጻሕፍት ናቸው። አራቱ ወንጌሎች እያንዳንዳቸው ልዩ እይታ እና ዓላማ አላቸው። ከትምህርት አንድ እስከ አምስት፥ ይህ ጥናት የእያንዳንዱን ወንጌል ታሪካዊ ዳራ፣ አወቃቀሩን፣ ዋና ይዘቶች እና ዋና ዋና ጭብጦችን ያብራራል። ከትምህርት ስድስት እስከ ስምንት፣ አንባቢዎች ዋና እና ዋና ያልሆኑ ጉዳዮችን ለመረዳት ይችሉ ዘንድ ሉቃስ ሲጽፍልን ያስቀመጣቸውን ዋና ዋና ነጥቦችን እና ለአንባቢዎቹ የሰጣቸውን ማዕቀፍ በአውዱ መሠረት እንመለከታለን። ይህ ኮርስ በ*ወንጌላት* እና *የሐዋርያት ሥራ* በተሰኙት በሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪስ በተዘጋጁት በሁለት ተከታታይ ቪዲዮዎች በመመሥረት በዶ/ር ፔት አልዊንሰን እና በ ዶ/ር ሀንስ ኤፍ ባየር አቅራቢነት የቀረበ ነው።

**ግቦች እና አላማዎች**

**ግቦች**

በዚህ ኮርስ፥ የሚከተሉትን ማከናወን እንፈልጋለን፦

1. ስለ እያንዳንዱ ወንጌላት ታሪካዊ ዳራ፣ ይዘቶች እና ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች፥ ቁልፍ ጭብጦችን እንደምትማሩ ተስፋ እናደርጋለን።
2. ወንጌላትን በምታጠኑበት ጊዜ ኢየሱስን የበለጠ ለማወቅ እና እሱን በታማኝነት ይበልጥ ለመከተል እንድታድጉ ተስፋ እናደርጋለን።
3. አራቱን ወንጌላት በምታጠኑበት ጊዜ የተማርካቸውን ትምህርቶች በራስህ ህይወት ላይ እንደምትተገብረው እና፥ በተለይም ኢየሱስን የበለጠ እንድታውቁት እና እሱን በታማኝነት ይበልጥ እንደምትከተሉት ተስፋ እናደርጋለን።
4. ስለ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ታሪካዊ ዳራ እና ይዘት ቁልፍ ትምህርቶችን ለማወቅ የትምህርቱን ሁሉንም ግብዓቶች እንደምትጠቀሙት ተስፋ እናደርጋለን።
5. የእግዚአብሔርን መንግስት በዓለም ላይ ለማስፋፋት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ በታላቅ ደስታ ለማድረግ እንደምትነሳሱ ተስፋ እናደርጋለን።
6. በሐዋርያት ሥራ ከምትማሩት ትምህርት የተነሳ በህይወታችሁ ላይ አንዳንድ ለውጦችን በማድረግ ምላሽ እንደምትሰጡ እና በተለይም ደግሞ በእግዚአብሔር መንግስት መስፋፋት ላይ ድርሻችሁን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እንደምታደርጉ ተስፋ እናደርጋለን።

**ዓላማዎች**

የሚከተለውን ስታደርጉ፥ ግቦቹ እንደተሟሉ ያሳያል፦

1. በፈተናዎች ላይ አጥጋቢ ውጤቶችን አግኙ። ይህንን ስታደርጉ የሚከተሉትን ማድረግ እንደምትችሉ ታሳያላችሁ፡-
    - የእያንዳንዱ ወንጌል ታሪካዊ ዳራ፣ ደራሲያቸውን፣ ተመልካቾቹን፣ የተጻፈበትን ጊዜ እና ዓላማን ጨምሮ ቁልፍ መረጃዎችን መለየት እንደምትችሉ
    - የአራቱን ወንጌላት መዋቅር እና ቁልፍ ይዘቶች መለየት እንደምትችሉ
    - የአራቱን ወንጌላት ዋና መሪ ሃሳቦች መለየት እንደምትችሉ
    - የሐዋርያት ሥራን ታሪካዊ ዳራ፣ መዋቅር፣ ይዘት እና ጭብጦች ቁልፍ መረጃዎችን መለየት እንደምትችሉ
2. ትምህርቱን በእራሳችሁ ህይወት ላይ እንዴት እንደተገበራችሁት እያሳያችሁ ለኢየሱስ እና ለእግዚአብሔርን መንግሥት መስፋፋት ያላችሁን ስሜት በመግለጽ የጥናት መመሪያዎችን አጠናቅቁ። በተለይም ደግሞ ትምህርቱ ኢየሱስን በተሻለ ሁኔታ እንድታውቁትና በበለጠ ታማኝነት እንድትከተሉት እንዴት እንደረዳችሁ እና እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት እንድትሠሩ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተበረታታችሁባቸውን  መንገዶች ግለጹ።

**የትምህርቱ ጨብጥ ሃሳብ ዝርዝር**

1. የወንጌላት መግቢያ
2. የማቴዎስ ወንጌል
3. የማርቆስ ወንጌል
4. የሉቃስ ወንጌል
5. የዮሐንስ ወንጌል
6. የሐዋርያት ሥራ ታሪካዊ ዳራ
7. የሐዋርያት ሥራ መዋቅር እና ይዘት
8. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ጭብጦች

**የቤት ስራ ማብራሪያዎች**

*የመልቲሚዲያ ትምህርቶች*

1. ቪዲዮውን በመመልከት፥ ኦዲዮውን በማዳመጥ ወይም፥ ጽሑፉን በማንበብ ***ትምህርቱን*** አጥኑ።
2. የእያንዳንዱን ትምህርት ***የጥናት መመሪያውን*** አጠናቅቁ። እነዚህ የጥናት መመሪያዎች በኦንላይን ለምትወስዱት አጭር ፈተናዎች እንድትዘጋጁ እና ትምህርቱን በእራሳችሁ ህይወት ላይ ተግባራዊ እንድታደርጉት ይረዱዋችኋል።
3. ለእያንዳንዱ ትምህርት በኦንላየን የሚወሰደውን ***የአጭር ጥያቄዎች ፈተና*** ተፈተኑ። የአጭር ጥያቄ ፈተናዎቹን የፈለጉትን ያህል ጊዜ መፈተን ይችላሉ፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ሙከራ መካከል የአንድ ሰአት ልዩነት መኖር አለበት። ከፍተኛው ነጥባችሁ ይፋዊ

ነጥባችሁ ይሆናል። ፅንሰ-ሀሳቦቹን በትክክል መረዳታችሁን ለማረጋገጥ በሳምንታዊው ውይይት ላይ ከመሳተፋችሁ በፊት ቢያንስ 80% ማሳካት እንዳለባችሁ እንመክራለን።

4. ከቡድናችሁ እና ከአሰልጣኛችሁ ጋር ***የውይይት መመሪያውን*** በመጠቀም፥ ሳምንታዊውን ***ውይይት*** ተካፈሉ። እነዚህ ውይይቶች የትምህርቱን ይዘት ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እና ፅንሰ-ሀሳቦቹን በህይወታችሁ እና በአገልግሎታችሁ ላይ በትክክል ለመተግበር ለመቻላችሁ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በቪዲዮ በሚተላለፉት ትምህርቶች ላይ የሚደረጉት ውይይቶች ቢያንስ አንድ ሰዓት እንዲቆይ እንመክራለን።
5. ***የአዲስ ኪዳን መሠረታዊ ትምህርቶች - የመጨረሻ ፈተና*** ውሰዱ። ፈተናውን ደግመህ የፈለከውን ያህል ጊዜ መውሰድ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ሙከራ መካከል የአንድ ሰአት ልዩነት መኖር አለበት። ኦፊሴላዊው ውጤታችሁ ከፍተኛው ነጥባችሁ ሲሆን የሚቀጥለውን ኮርስ ከመቀጠላችሁ በፊት ቢያንስ 80% ማግኘት እንዳለባችሁ እንመክራለን።

*የማስተማር ባጅ*

1. በየሳምንቱ ***የማስተማር ባጅ መመሪያዎችን*** ለማጥናት አንድ ሰዓት መስጠት አለባችሁ። ይህን አስፈላጊ የአገልግሎት ክህሎት ለማዳበር በምትፈልግበት ጊዜ ይህ ከአንድ እስከ ሁለት ገጽ ያለው መመሪያ ለአሰልጣኝህ አጠቃላይ መመሪያ ይሰጣል።
2. በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ፣ በሳምንቱ ውስጥ ያለህን አንድ ሰዓት በማስተማር ባጅ መመሪያዎች ውስጥ ***የውይይት ርዕሶች*** ሂድባቸው።
3. በቡድን የውይይት ጊዜያት ጠንካራ መሰረት ከተጣለ፥ ቀሪዎቹን ሳምንታት የባጅ ***የትግበራ እርምጃዎች*** በማጥናት አሳልፍ።
4. ከባጅ መመሪያዎች አንጻር የትግበራ እርምጃዎች መጠናቀቅ አሰልጣኙ ከወሰነ በኋላ ባጁን ትሸለማለማላችሁ። ሁሉም ባጆች በተማሪዎች "የጀርባ ቦርሳ" ላይ ቦንላየን ክፍል ውስጥ ይታያሉ።

**ውጤት**

የመጨረሻው ውጤት እንደሚከተለው ይሰላል፥

1. 30 ነጥብ የሚያዘው በክፍሉ ውስጥ ከተደረገው ሌክቸር ነው።
2. የመጨረሻ ፈተና ከሌክቸሩ 100 ነጥብ ይይዛል።
3. የማስተማር ባጅ ሪፖርት በውጤትዎ ላይ ለውጥ አያመጣም ነገር ግን ኮርሱን ለማጠናቀቅ መቅረብ አለበት።

*ከ80% በላይ አጠቃላይ የኮርስ ውጤት ለማለፍያ ነጥብ ይቆጠራል።*